# ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

መለየት ተሳነኝ ፣ ትላንትን ከዛሬ
አልነጋም ገና ነው ፣ ምን ነካት አገሬ ?
ወንጀል አልባ ታስሮ ፣ ግፈኛ ሲፏልል
እንዲህ ሆነ መሰል ፣ ያገራችን ባህል
ወይንስ ያንድ ሳንቲም ፣ ሁለት ገጾች ናቸው
ቤት ለንቦሳ ብለን ፣ የተቀበልናቸው ?
ይሆን በመደመር ፣ ሰበብ ተመካኝቶ
ጉልበቱን ፈትሾ ፣ አቅሙን ገምቶ?
እኔን ግራ ገባኝ ፣ ምን ይሆን ሚስጥሩ
ወንጀለኛን አዝሎ ፣ ማለት እሹሩሩ ።

ያልሰረቀን አስሮ ፣ ያልገደለን አስሮ
ፍትህን ሲጠይቅ ፣ እያሰማ እሮሮ
ያላዩ ይመስል ፣ እንዳልሰማ ጆሮ
በፍርድ ማንገላታት ፣ ሺ ግዜ ቀጠሮ
ምን ልዩነት አለው ፣ አምናና ዘንድሮ
ስጋው የተበላ ፣ አጥንቱ ተሰብሮ
ዛሬም ይንገላታል ፣ ገዳዩ ተከብሮ ።

የማይደመርን ፣ እንደምር ብላችሁ
ከእባብ እንቁላል ፣ እርግብን ናፍቃችሁ
ምናባዊ ተስፋ ፣ ከንቱ ሰንቃችሁ
ምትሃታዊ ክስተት ፣ ይፈጠር መስሏችሁ
ለናንተም መሳደድ ፣ እንዳይመጣባችሁ
ህዝቡንም በከፋ ፣ ታስፈጁታላችሁ ።

የማይደፈሩ ፣ የማይገሰሱ
ሳንሰማና ሳናውቅ ፣ ባገር የነገሱ
ትንሹን ትልቁን ፣ ሁሉን ያስለቀሱ
ዛሬም በዜጎች ላይ ፣ ሞት እየደገሱ
መገደል መሳደድ ፣ አልመጣ በነሱ
እነሱን ለመያዝ ፣ እንዳይገሰግሱ
ሲያመነቱ እያየን ፣ መሄድ ወደነሱ
ድምር ነው ዘመኑ ፣ ይሉናል ታገሱ
ትዕግስት እስከ መቼ ፣ አገር እስኪያፈርሱ ?

በህልሜ እንዳልል ፣ የሰማሁት በውኔ
እልፍ የቆረጠመ ፣ ደም መጣጭ ወያኔ
ወደር የሌለውን ፣ በግፍ በጭካኔ
ካርቱም ተጎልቶ ፣ ቁጭ ብሎ መድህኔ
አመለጠ ማለት ፣ ይህን አረመኔ
ከመርዶም በላይ ነው ፣ ይሄስ ለወገኔ
እንዲህ ያለ ተረት ፣ አይጥመኝም ለኔ ።

እስቲ ሰው ሁኑና ፣ እንደሰው እናውራ
መተዛዘን ነው ወይ ፣ እንደ ባልንጀራ ?
ግፍና በደልን ፣ ባገር ላይ የሰራ
መቀሌ ከትሞ ፣ ሲደነፋ ጉራ
ደም እያፋሰሰ ፣ እየሳለ ካራ
ተንኮላቸው ዛሬም ፣ ካልሆነ የሚያባራ
እኛ የማናውቀው ፣ ካለም የሚያስፈራ
እውነቱን አውቀነው ፣ እንስራ በጋራ
አታድበስብሱብን ፣ መንገዳችሁ ይጥራ ።

አገሪቷን ሲያል ፣ ያረገ ገሃነም
ድንበር እየጣሰ ፣ እየወጣ ሲተም
ይሄንን ለመግታት ፣ ምነው አይታለም ?
ዛሬ የሰማነው ፣ ቧልቱም አይደገም
ሌላ ተረት አምጡ ፣ የዛሬው ይታረም
አልሆነላችሁም ፣ ከቀን ጅቦች መቅደም
ሌላ እስከምንሰማ ፣ በዚህ እንደመም ።

ገዳይ አገር ለቆ ፣ በወጣ ባሙቱ
የማይመስል ነገር ፣ እንዲያው ያላባቱ
ልናስረው ነበረ ፣ ብሎ መደንፋቱ
ውሸቱም አይሰምር ፣ አለባለቤቱ
ዳግም እንዳትነግሩን ፣ ሌላ መላ ምቱ
የማይጥም ጨዋታ ፣ አልሰራም ለወቅቱ
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ፣ የውዳሴ ከንቱ ።

ታዛቢው

August 22, 2018